# ነገረ ሰንደቅ ዓላማ

## በኪዳነ ማርያም ግርማይ

ይህችን ጽሑፍ ለማዘጋጀት ያነሳሳኝ ዋና ጉዳይ በማወቅም ባለማወቅም አንዳንድ ሰዎች ባንዴራን በተመለከተ የሚነዙትን ውዥንብር አሳስቦኝ ነው። እናም፡- ሰው "የያዘውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም" እንዲሉ ስለ ባንዴራ ያለኝን ግንዛቤ በጽሑፍ ለመጋራት ነው።

ይህችን አጭር ጽሑፍ እንደ መነሻ ሓሳብ ወስደን የኢትዮጵያ ባንዴራ የሄደችበትን ታሪካዊ ጉዞ ስንመረምረውና የኢትዮጵያ ሕዝብ በየክልሉ ተወያይቶ በገዛ ባንዴራው ላይ ማስተካከያ ስላደረገበት ባንዴራችን ተለወጠች "ኡ! ኡ! "እሪ! እዝን!! ያሰኛልን? በመሠረቱ ባንዴራችን ተለውጣለችን? ተለውጣለች ከተባለ'ስ ደግሞ ከምን ወደ ምን? ምን ዓይነት ለውጥ ነው? የዓይነት? የመጠን? መሠረታዊው ኅብሯ፡- አረንጓዴው፣ ብጫውና ቀዩ መልኳ ተለውጧልን? አልተለወጠም ከተባለ ደግሞ ታድያ ባንዴራችን ምን ሆነች? በሚሉ መሠረተ ሐሳቦች ላይ ጥያቄ አንስቶ መማማር ይቻላልና እንሂድበት፡-

በመሠረቱ ብሔራዊ ባንዴራ በተወሰነ መልክዐ ምድር የሚገኙትን ሀገሮችና በየአገሩ የሚኖሩትን ዜጎች የሚወክል ልዩ መለያ ከመሆን ያለፈ ሌላ ሕቡእ ምሥጢር የለውም። ባንዴራ የሰው እውቀትና የፈጠራ ችሎታ የፈጠረው፣ የሚዳሰስ፣ የሚጨበጥ የአንድ ልዑላዊ ሕዝብ ሀገራዊ የማንነት ልዩ ሥእላዊ መገለጫ ነው። ሰንደቅ ዓላማ የነፃነትና ልዑላዊነት ታሪክ፣ የሥነ_ሕዝብና ማኅበራዊ ሕይወት እንዲሁም የሕዝቦች ማኅበራዊ ትስስርና ታሪክ ወ.ዘ.ተ ሁሉም አንድ ላይ በውህደት የሚገለፁበት ጥልቅ የታሪክ መድበል ነው። እንዲህ ማለት ደግሞ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የማናቸውም ልዑላዊ ሕዝብ ሁሉ የነፃነቱ አካላዊ ተምሳሌት ባንዴራው ነው ማለት ነው።

ነገር ግን የሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ በአጠቃላይ ሲታይ በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም መሠረታዊ ትርጉም ማጣቱ ጥርጥር የለውም። ምክንያቱም ባንዴራ ከጥንት ይዞት የመጣውን የሀገሮችና የሕዝቦች የነፃንትና የልዑላዊነት ተምሳሌት በቅኝ ገዢዎች፣ በቀጥተኛውና እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ምክንያት ተጨባጭ ሕዝባዊ የባንዲራነት ክብሩ አጥቷል። ቀጥተኛው ቅኝ ግዛት ባስከተለው ጣጣ ምክንያትም ብዙ ሀገሮች ጥንታዊ የተናጠል ወይም የጋርዮሽ ሀገራዊ ልዑላዊነታቸውን ያጡና በቅኝ ግዛት ተፅዕኖ አንድ ላይ ተጨፍልቀው በመጠቃለል ወይም ተገደው በመለያየት አዲስ ቅኝ ግዛታዊ ታሪክና ስም የያዙበትን ሁኔታ እናያለን። ለዚሁም ከኢትዮጵያ በስተቀር በዓለም ዙርያ አንድ ሁለት ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉ ለስሙ ባንዴራ እያውለበለቡ ነገር ግን ጠቅልሎ ሀገራዊ ክብራቸውን፣ ልዑላዊነታቸውና ነፃነታቸውን ያጡ፤ ሀብታቸው ሁሉ ተዘርፎ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ እሴታቸው ተመዝብሮ የተወሰደባቸው አገሮች እጅግ በርካታ ናቸው።

እነዚህ የቅኝ ግዛት ሰለባ የሆኑት ሕዝቦች ባንዴራ (ሰንደቅ ዓላማ) ስላውለበለቡ ብቻ ነጻና ልዑላዊ ሕዝቦች ናቸው ማለት አይቻልም። በዚህ ሐተታ መሠረት ባንዴራ ታሪካዊ ቅርስ ወይም ውርስ ብቻ ሆኖ ቀርቷል ማለት ይቻላል። ለምሳሌ ባንዲራ እንደ ምልክትነቱ ከአንድ ሀገር ወደ ሌላኛው አጐራባች ሀገር ስትሄድ በሁለቱም ሀገሮች በኩል በየደንበሮቻቸው ላይ ባንዴራ ተተክሎ ይታያል። ትርጉሙም በአንዱ በኩል ባለችው ሀገር እስከዚህ የእኔ ቦታ ነው የሚል ሲሆን በሌላኛው ወገን ባለችው ሀገር በኩልም ከዚህ ጀምሮ ያለው ምድር ደግሞ የእኔ ሀገር ነው የሚል ነው። እንዲሁም ኤምባሲዎችና ሌሎች የውጭ ዲፕሎማቶች፣ የሀገር ውስጥ መሥሪያ ቤቶችም እንዲሁ ማንነታቸውን በባንዴራ ይገልጣሉ። በአጠቃላይ ባንዴራ ክቡር ነው፤ ጥቅሙና ትርጉምም በዚህ ዙርያ ይጠቃለላል።

የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የማንኛውም አገር ባንዴራ፣ የሁሉም አገሮች ሰንደቅ ዓላማ የተሠራው ከጨርቅና ጨርቃ ጨርቅ ብቻ ነው። በወርቅና በዕንቍ የተሠራ ባንዴራ ግን የለም። ስለዚህ ባንዴራን ባንዴራ ያሰኘው በጨርቁ ላይ የተሠራው ትርጉም ያለው ምስል (Icon) ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያ ባንዴራ በሦስት፡- አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ ኅብረ ቀለማት በጨርቅ ላይ ተስለውበት የሚውለበለብ ኅብራዊ ሰንደቅ ዓላማ ኢትዮጵያን ይወክላል። ባንዴራ ከዚህ ውጭ ሌላ ምንም ሕቡእ መለኮታዊ ትርጉም የለውም።

ሕዝባችን ለሀገሩ፣ ለባንዴራውና ለታሪካዊ ነጻነቱ ያለውን ቀናኢነት፣ ፍቅርና ክብር ስለሚያውቁ ይህንንም የሕዝብ ስሜት ሰርቀው በመውሰድ ጥቂት ብልጣ ብልጥ ሰዎች ባንዴራችንን ከባንዴራነቷ ውጭ አውርደው ሊጠቀሙባት፣ እንደ አምልኮ ጣዖትም ሊመፃደቁባት ሁል ጊዜ ይዳዳቸዋል። ስለሆነም ብላጣ-ብልጦቹ ባንዴራ በቀስተዳማና ምሳሌ በነገረ መለኮት ከሰማይ ወርዳ ዱብ እንዳለች የፈጠራ አልቧልታዊና መርዘኛ ወሬአቸውን ይነዛሉ። ምሳሌነቱም በሦስት ሥላሴ፡- በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ አምሳል ለአባቶቻችን እንደ አንድ ኦርቶዶክሳዊ መንፈሳዊ ፀጋና በረከት ከሰማይ እንደ ወረደች አስመስለው የፈጠራ ታሪክ ይተርካሉ። ብልጣ ብልጦችና አጭበርባሪዎች ሁሉ ይህንን ከእውነት የራቀና የተዛባ የሐሳባውያን የማደናቀርያ ዜና ዕብደትና የዕንቆቅልሽ ትርጉም በመስጠት ከእውነተኛው ሀገራዊ ባንዴራነቷዋ በላይ ዘልቀው በመሄድ እንሆ ሲፈልጉ እንደ ምጸለያ፣ ሲፈልጉም እንደ መጠንቈያና ማታለያ ይጠቀሙባታል።

ከዚያም አልፎ ባንዴራዋን ሲፈልጉ የአስክሬን መሸፈኛ፣ ሲፈልጉም የታቦት ማጐናፀፍያ፣ ሲፈልጉም የመስቀልና የመጽሐፍ መሸፈኛ፣ ሲፈልጉ ለማንኛውም ዕቃ እንደ ማንጠልጠያ ሲያደርጓት ይታያሉ። ይህም መደፈሯን እንጂ ምንም ሁኔታ ክብሯን ወይም ፍቅሯን አያመለክትም። በኢትዮጵያ ባንዴራ ላይ ያልደረሰ እንግልትና መንከራተት የለም ቢባል አልተጋነነም። በመሆኑም በዚህ ሁኔታ ባንዴራችን ሀገራዊ ባንዴራነት ክብሯ ተደፍሯል ቢባል ስሕተት አይሆንም። ይህንን ሁኔታና ስጋት ተከትሎ ዜጎች ሁሉ ባንዴራቸውን አስመልክተው በወቅቱ ጥያቄያቸውን በሕግ ሊስተጋቡ ችለዋል። ከዚህ በመነሣት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕዝበ ውሳኔው መሠረት ስለ ባንዴራ በየክልሉ በሰፋት ከተወያየበት በኋላ በሕገ መንግሥቱ የተካተተ ዘላቂ መፍትሔ ማስቀመጡ ይታወሳል። ይህንን በተመለከተ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ሕገ መንግሥት ከገጽ ፯ አንብቦ መረዳት ይቻላል።

በጥንት ዘመን “ባንዴራችን እንዴት አደረች” ይባል ነበር ይባላል። እንዲህ ማለት ደግሞ የሀገር ሁኔታ፡፣ ሰላምና ፀፅታን በተመለከተ በባንዴራዋ መውለብለብ ይታወቅ ነበር ማለት ነው። ባንዴራዋ እየተውለበለበች ለሕዝብ ተፈላጊና ወቅታዊ መልእክት ወይም አዋጅ በአየር ታስተላልፍ ነበር ማለት ነው።

ከባንዴራዋ ባህርየ ሕብረ ቀለማት ጋራ አብሮ የሚሄድ በሰዎች ቅፅበታዊ የዓይን እይታ (Eye wink) መሠረት ባንዴራው በአረንጓዴው ክፍል ስለ ልማትና ዕድገት፣ በብጫው ስለ ሰላም፣ በቀዩ ክፍል ደግሞ ስለ ጀግንነትና ነጻነት ነው የሚውለበለበው የሚል ትርጉም አለው። ባንዴራ ከፍ ብላ ስትሰቀልና ዝቅ-ወረድ ብላ ስትሰቀልም የየራሱ ልዩ ትርጉምና መልእክት አለው። ባንዴራችን እንዴት አደረች ያሰኛቸውም ያ ነው። ሕዝብ ያመነበትና ተቀባይነት ያለው የባንዴራ ትርጉም ይህ ነው። ከዚህ ውጭ ባንዴራ ለሌላ ነገር ማዋል፣ ሌላ ቀለም መቅባትና ሌላ ትርጉም መሥጠት በምንም ተአምር ትክክል አይሆንም። ባንዴራ ሕዝባዊት ወይም የሁሉም ዜጎች የጋራ ንብረት ናት። በመሆኑም ሕዝብ (ዜጎች በሙሉ) የገዛ ባንዴራቸውን የመለውጥ ወይም የማስተካከል ወይም የመተቸት መብት አላቸው። ይህ መብት ደግሞ ምን ጊዜም ቢሆን የነሱና የእነሱ ብቻ ነው። ስለዚህ የተወሰኑ ግል ሰቦች ወይም ድርጅቶች ስለ ባንዴራ ይበልጥ ተቆርቋሪ መስለው በመቅረብ፣ ባንዴራዋን በሰንደቅ ዓላማነት ከተሰቀለችበት መድረክ አውርደው ለፖለቲካ ጥቅም ሊያውሏት አይገባም።

ባለቤቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሀገሩ ባንዴራ ላይ የሚደረገውን ጋጠ ወጥ ከታዘበ በኋላ ይህች ባንዲራ የኛ፣ የሕዝብ ሰንደቅ ዓላማ ናት ወይ? ወይስ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እንደ መስቀልና እንደ ሌሎች ንዋየ ቅዱሳት የቤተ ክርስቲያን መገልገያ እቃ? በሚል ስጋትና ጥርጣሬ ቢጠይቅ ጥያቄው ተገቢና መመለስ ያለበት መሠረታዊ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ጥያቄ ነው።

ነገር ግን ሕጋዊነት ባለውና በሌሎች አገሮች እንደ ሚደረገው ሁሉ መንፈሳውያንም ዓለማውያንም ድርጅቶች (Institutions) ሰንደቅ ዓላማዋን በሀገራዊ ባንዴራነቷ መልኩ የመጠቀምና በሥሯ የመጠለል ሕጋዊና ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው ሁሌ የተከበረ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ከዚህ ውጭ ከሰንደቅ ዓላማ በታች ዝቅ አድርጎ በማውረድ ባንዴራዋን እንደ ግል ዕቃ ማንገላታትና ክብሯን ማሳነስ ግን ነውር ነው ማለት ብቻ ሳይሆን ሕጋዊነትም የለውም። በዚሁ ትንታኔ መሠረት ባንዴራ የአማንያን ብቻ ሳይሆን

የዜጎች ሁሉ ሀገራዊ ባንዴራ ናት። ይህች ባንዴራ የማኽል አገር፣ የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የአክሱማውያን ወይም የትግራይ ብቻ፣ የክርስቲያኑ ወይም የሞስሊሙ ሕዝብ ብቻም አይደለችም። ባንዴራ ግል ሰቦች ወይም ድርጅቶች በአቀማመጥም ሆነ በሕብረ ቀለም ላይ እንደ ፈለጉ የሚያደርጓት መሆን አልነበረባትም። ይህች ሀገራዊ ሕዝባዊ ባንዲራ በሁኔታ፣ በምክንያት፣ በጊዜ ወይም መንግሥታት ወይም ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ሲለዋወጡ መለወጥ ከማይገባቸውና ዘወትር ቋሚ ሆኖው መኖር ከሚገባቸው ነገሮች ባንዴራ አንዱ ናት።

ይህች የዓለም ሕዝብ የሚያውቃት ጥንታዊት የኢትዮጵያ ባንዴራ በሦስት ኅብረ ቀለማት (አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ) ባህርይዋ ሳይለወጥ በተለያዩ ጊዜያት መጠነኛ ለውጥ የተደረገባት ሁኔታ እንዳለ ይተረካል።

---

፬ኛ. በጥንት ዘመን አባቶቻችን ሁኔታዎች ሲለዋወጡባቸው ሁኔታዎቹን ለሕዝብ ለማሳወቅ ቀዩንና አረንጓዴውን በማዛወር (በማቀያየር) ሰንደቅ ዓላማ ያውለበልቡ እንደ ነበር ኢትዮጵያዊው ትውፊታዊ



ታሪክ ይናገራል። እሱም በአብዛኛው ሀገር ሰላም ስትሆን አረንጓደውን ከላይ፣ ብጫውንም በማኽልና ቀዩ ከሥር ተደርጎ ሲሰቀል እንደ ነበረ የነገራል።

---

፭ኛ. አገር ጠርነት ላይ ስትሆን ደግሞ እንዲሁ ቀዩ ከላይ፣ ብጫው በማኽል አረንጓዴው ደግሞ ከሥር



ተደርጎ ባንዴራ እንዲህ ስትውለበለብ እንደ ነበረች ትውፊታዊ ታሪክ ይተርካል። ሰንደቅ ዓላማ እንዲህ ከተውለበለበች ደግሞ ሰንደቅ ዓላማዋ የጦርነት ባንዴራ ሆነች ማለት ነው።

---

፮ኛ. በዘመነ አፄ ኃይለ ሥላሴ ደግሞ በባንዴራው ላይ "ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ" በሚል ዘውድ በጫነ



የአንበሳ ምስል (personal emblem) ተለጥፎበት ይታያል። በተለይ ይህች መስቀልና ባንዴራን የያዘች ዓይነት ሰንደቅ ዓላማ ዘውዳውያን መንግሥታትና ቤተ ክህነት በጋራ ጥቅም ተቀናጅተው ይጠቀሙባት የነበረችው ዓይነት ባንዴራ ናት። በዚሁ ሁኔታ ሲታይ ባንዴራችን ሕዝባዊትና ሀገራዊት ሰንደቅ ዓላማ መሆኗ ቀርቶ አፄ ኃይለ ሥላሴ ባንዴራዋን እነደ ሀገራዊ ሕዝባዊ ባንዴራ ሳትሆን



ለሚመኩበት የራሳቸው አይሁዳዊ ዘራቸውና ለአይደፈሬው መለኮታዊ በትረ ሥልጣናቸው ኃያልነት መገለጫ እንዳደረጓት ከቅርብ ጊዜ ታሪክና ባንዴራዋ ላይ ከተለጣጠፉት ነገሮች ሁኔታዎቹን መገንዘብ ይቻላል።

---

፯ኛ. የኢትዮጵያ ባንዴራ በደርግ ዘመነ መንግሥት፡- ደርግ በባንዴራዋ ላይ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ በከፋ መልኩ ማርክሰ ሌኒናዊ ኮሚንስትዊ የተውሶ ርእዮተ ዓለማውና ፀረ ሕዝብ ፋሽሽታዊ ፍልስፍናውን



ለማንፀባረቅ ሶሻሊስታዊ አርማውን በኢትዮጵያ ባንዴራ ላይ በመለጠፍ የራሱ (Personal property) አድርጓት ሲኖር ነበር። ደርግ ባንዴራችንን የግሉ ከማድረጉ ባሻገር ደርግ በገዛ ሥልጣኑ ሕዝብ ሳያማክር ባንዴራዋን ለውጭ አሳልፎ እንደ መስጠትና እንደ ዐቢይ ክሕደት የሚቆጠር ወንጀል ሠርቷል። ደርጋዊ መንግሥት ከተሸነፈ በኋላ ግን ያ ሁሉ በባንዴራዋ ላይ ሲደረግ የነበረው የህጻናት ጨወታ ሁሉ ላንዴና ለመጨረሻ አክትሟል።

---

፰ኛ. በዘመነ አፄ ኃይለ ሥላሴ በኢትዮጵያ በአጠቃላይ ማኅበራዊ ችግሮች እየተባባሱ መምጣት፣ የምጣኔ ሃብት ክፍፍል ኢፍትሐዊነት፣ የሕዝቦች እኩልነት እጦትና የመሬት ለአራሹ ጥያቄ በጊዜው ካለማስተናገድና የዲሞክራሲ የሕዝብ ጥያቄዎች ተገቢ በሆነ መንገድ ካለመመለሳቸው የተነሳ ችግሮች ክፉኛ ተባብሰዋል። በተለይ የ፷፮ ዓ/ም በኢትዮጵያ ታላቁ አብዮት እንዲፈነዳና ሰደዱ እንዲቀጣጠል እነዚህ መሠረታዊያን ምክንያቶች ነበሩ። ባንዴራችንን የሕዝብ ባንዴራ የማድረጉ ጉዳይም አብሮ ተነስቷል።

---

በዚህ መሠረታዊ የአብዮት መነሻ ውስጥ ከተካተቱት ነገሮች አንዱ ይህች ባንዴራ እስከ ዛሬ ድረስ ሁላችንን በእኩልነት አልወከልችም። የተውስኑ የንጉሣውያን ቤተ ሰቦች የፈለጉትን ዓይነት ምሥል በባንዴራዋ ላይ በመለጠፍ እንደ ፈለጉ ሲያድርጓት ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲህ አለ፡- በመራራው ትግል ባገኘነው ድል መሠረት ፌዴራላዊ

መንግሥት በጋራ መሥርተን፣ በእኩልነት አብረን ተከባብረን የምንኖር ከሆነ፣ እንሆ አስተማማኝ በሆነ መልኩ ሕጋዊ ሰነድ ፈጥረን ውል እንሰር፤ ውላችን በሕገ መንግሥት ይረጋገጥ። በዚሁ የጋራ ሕጋዊ ሰነድ ውስጥም ይህች ጥንታዊት ኢትዮጵያዊት ባንዴራ የእኛ የሕዝብ ለመሆኗ፣ እኛን ለመወከሏና ለሕዝባዊነቷ ማረጋገጫ ምልክት፣ በባንዴራዋ ላይ አንድ ሕዝባዊ ትርጉም ያለው ማንኛውም ኃይል፣ ድርጅት ወይም ሰው፣ ሕዝብ ሳያማክር የማይለውጠው ቋሚ ምልክት ማስቀመጥ አለብን በሚል ቃል ኪዳን እንሆ ሕዝባዊ ትርጉም ያለው ምልክት ለማስቀመጥ ተችሏል።

ይህም በኢትዮጵያ አንድ ትልቅ ታሪካዊ ፍጻሜ ነው። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ በየክልላቸው በተናጠል፣ እንዲሁም በአጠቃላይ በሀገር ደረጃ፣ ተወያይተውበት ለጋራ ጥቅም ተማምነውበት



ይወክለናል፣ ያስተባብረናል ብለው የመረጡትን እንሆ አንድ ቋሚ ምልክት መርጠው በገዛ በባንዴራቸው ላይ ለማስቀመጥ በቅተዋል። በዚሁም መብታቸውን ለማስከበር አበክረው ጠይቀዋል ብቻ ሳይሆን ታግለዋል፣ ታግለውም ለድል በቅተዋል። በተለይ ሕገ መንግሥቱ በሚረቀቅበት ጊዜ በ፲፱፻፹፭ ዓ/ም በተደራጀ መልኩ በሽግግሩ መንግሥት ወቅት የባንዴራው ጉዳይ ዘላቂ መፍትሔ አግኝቷል። የባንዴራው ጉዳይ በዚሁ ውጣ ውረድ የትግል ጉዞውን ተጉዞ ፌዴራላዊ ትርጉሙ በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ተብራርቶ ከዚህ በላይ የሚታየው ሰንደቅ ዓላማ እንሆ ሕዝባዊ፣ ሀገራዊ ፌዴራላዊ ባንዴራ ለመሆን ችሏል።

ባንዴራን በተመለከተ የተደረገው ሕዝበ ውሳኔ በውስጡ ታላቅ ቁም-ነገርና ሕዝባዊ መልእክት አለው። በመጀመሪያ፡- አረንጓዴው፣ ብጫና ቀይ ኢትዮጵያዊ ኅብረ ቀለም ባህርይዋ አልተለወጠም፤ ካለመለወጡም በላይ እነዚህ ቀለማት በመላ አፍሪቃ የነጻነት፣ የኅብረ ብዙኀነት፣ የልዩነት፣ የውህደትና የአንድነት ምልክት ሆኖዋል፤ ከብዙዎች አፍሪቃውያን ወንድሞቻችን ጋራ እንጋራዋለን። ይህች አረንጓዴ፣ ብጫና ቀይ ባንዴራ ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን ሌሎች ብዙ የአፍሪካ ሀገሮችም በተለያየ አቀማመጥና ዘዴ በባንዴራነት ይጠቀሙበታል ማለት ነው። ስለዚህ ምልክቱ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለይተው ለማያውቁ ሰዎች ለማሳወቅ ይረዳል።

በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ ለውይይት ያኽል የተቀመጡትን መሠረታውያን ጥያቄዎች በእንድምታዊ መልኩ በመመለስ ጽሑፉን ልቋጨው ፍቀዱልኝ። በሕዝበ ውሳኔው መሠረት በኢትዮጵያ ባንዴራ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስቀመጠው ልዩ ምልክት መከበር ያለበት፣ ሕዝብ ክብሬን አትንኩብኝ፣ ካለፈቃዴ ባንዴራየን አትለውጡብኝ የሚል፣ እንደ ማኅተም (As a great seal or Icon) የሚቆጠር ክቡር የሕዝብ ቃል ነው። ከዚህ ውጭ ባንዴራችን ተለወጠች፣ "እሪ! …ኡ! ኡ! የሚያስኝ ልቅሶና ኡ! ኡታዊ ሁኔታ አያስፈልግም። ስለ ትርጉሙ በሕገ መንግሥት የተጻፈ ስለሆነ እዚህ ላይ መድገሙ አስፈላጊ መስሎ ብዙም አልታየኝም።

እርግጠኛ ሳይሆኑ ስለ አገራችን ባንዴራ ይብልጥ ልዩ ተቆርቋሪ በመምሰል ባለማወቅ ወይም አውቆ ለፖለቲካዊ ድርጅታዊ/ግላዊ ጠቀሜታ ተብሎ የሚረጨው የአዞ እንባና አልቧልታ ወሬ ሁሉ ይቁም። ብልጣ ብልጦቹ ዓይነ አድርቅ የአዞ እንባቸውን በከንቱ ልቅሶ አይፍጁ። የባንዴራ ነገር አብቅቶለታል፤ በሕዝበ ውሳኔ ተቋጭቷል፤ ላንዴና ለመጨረሻ በሕዝብ ቃል ታትሟል። ባለቤቱ ሕዝብ ተረክቧታል፤ የሕዝብ ቃል ከብረት አጥር የጠነከረ ነው፤ እናም፡- ይህ ሕዝባዊ ተሳትፎና ታሪካዊ ሕዝበ ውሳኔ፣ ባንዴራችን ብሕዝብ ቃል ---በበረት የችቦ አጥር ታጥራለች፤ ለዘላለምም ከብራለች የሚያስብል እንጂ ባንዴራችን ተለወጠች የሚያስብል አሻሚ ፍች ወይም ትርጉም የለውም። ባንዴራችን ጥንታዊ መልኳ፡- አረንጓዴው፣ ብጫውና ቀይ ኅብሯ አልተለወጠም፤ ምንጊዜም ቢሆን ታሪካዊት ወርሳችንና ቅርሳችን ናትና አትለወጥምም።

ጽሑፌን ለምታነቡ፣ ሓሳቤን ለምትጋሩኝ ክቡራንና ክቡራት ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሁሉ!! ክብርና ምስጋና ይሁን። እኔ ጸሐፊና አዋቂ ሁኜ ሳይሆን፣ ሰው "የያዘውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም" በሚል ድፍረት ነው ይህችን የጫርኳት። ስለዚህ በጽሑፉም "ከሰው ስሕተት ከብረት ዝገት" ሁሌ አይታጣምና ድፍረቴን በይቅርታ ስሕተቴንም በእርምት እንደ ምታልፉኝ እርግጠኛ ነኝ። አመስግናለሁ!!

ኪዳነ ማርያም ግርማይ
ዘእም ብሔረ ቅዱስ ዲጎ፥ አሜሪካ
፱፥ ፱፥ ፳፻ወ፲፱ቱ ዓ/ም